# አውቀው በድፍረት ሳያውቁ በስህተት ለፈጸሙት ሀጢያት ይቅር በላቸው ከማለት በስተቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

**በእውነቱ ዘለቀ**

Tigrai Online Dec. 29, 2016

አቶ ብርሀነ ካህሳይ A Riposte to Gedu's Foot Soldiers (ለገዱ እግረኛ ወታደሮች ስድብ ወይም ሂሰ ፈጣን ምላሽ) በሚል ርእስ የጻፉውን መልስ በትግራይ ኦን ላይን ድረ-ገጽ ላይ ታትሞ ሳነብ በድጋሜ ተገረምሁኝ፣ መቼም አቶ ብርሀነ የእንግሊዘኛ ቋንቋን ተጠቅሞ በመጻፉ ራሱን ከሌላው የተሻለ አዋቂ አድርጎ የሚቆጥር ሰው እንደሆነ መገመት አይከብድም፣ ለዚህም ይመስለኛል ምናልባትም በትግርኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ ሊገልጣቸው የማይፈልጋቸውን ሀሳቦች/ቃላቶች ሳይቀር ይህንን የባዕድ ቋንቋ በመጠቀም መረን የለቀቀና በቂም በቀል እንዲሁም በጥላቻ መንፈስ የተሞላ ውስጡን ያለ ይሉኝታ ገልብጦ ሊያሳየን የሞከረው፡፡

የሚገርመው ነገር ደግሞ አብዛኛው ተደራሲው/አንባቢው እሱ ግለሰቦችን ለመወንጀል እየተጠቀመበት ያለውንና እንደ እውቀት መለኪያ አድርጎ የወሰደውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ሳይሆን ትግርኛና አማርኛን የሚያነብ መሆኑን መዘንጋቱ ነው፡፡ ወይስ ለተወሰኑ ልሂቃን ፖለቲካዊ ፍጆታ ታስቦ የቀረበ ማደናገሪያ/መሰዳደቢያ (Medium of obstruction/insulting) አድርጎ ሊጠቀምበት ፈልጎ ይሆን? የዚህኛው ጽሁፍ አብዛኛው ክፍል ከባለፈው ጋር የሚመሳሰል ሲሆን እኔን ጨምሮ የእሱን ሀሳብ በማስረጃ አስደግፈው ለመገዳደር በሞከሩ ሁለት ሰዎች መነሻነት የብአዴን አባላት አሁንም በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን ካሰመረ በኋላ የገዱንም ወንጀለኝነት ብዙ ሰው እንደሚያምንበት አድርጎ ለመግለጽ ይሞክራል፣ የዚህ አይነቱ የተሳሳተ መደምምሚያ ከሎጂክ አንጻር ሲፈተሽ Hesty Generalization ይባላል፡፡

አቶ ብርሀነ ያለመብሰሉና የቂልነቱ ማሳያ ደግሞ ወታደርነትን እንደ መስደቢያ ቃላት አድርጎ በርዕስነት መጠቀሙ ሲሆን ለሀገሩና ለአመነበት አላማ ግንባር ቀደም ወታደር ሆኖ መሰለፍና መስዋዕትነትም መክፈል ትልቅ ከበሬታን የሚያስገኝ የስራ መስክ እንጂ እሱ በአሉታዊ መልኩ ሊጠቀምበት እንደሞከረው መሰዳደቢያ ሊሆን አለመቻሉን ለሚገነዘብ ሰው የሰውየውን ባዶነት ወይም ግልብነት በግልጽ እንደሚያሳብቅ መረዳት አይቸግረውም፡፡

ለመሆኑ አቶ ብርሀነ ከ95% በላይ የሚሆነው ከፍተኛ አመራር/ጀነራሎች/ የህወሀት ነባር ታጋዮች እንደሆኑ የሚነገርለት የመከላከያ ሰራዊት የወታደሮች ስብስብ መሆኑን ረስተኸው ይሆን ይህን ለማለት የደፈርኸው? ወይስ ወታደርነት ለትግራይ ተወላጆችና ለህወሀት ታጋዮች ሲሆን ትርጉሙን ቀይሮ የተለየ ክብር ይሰጠዋል ብለህ ስለምታምን ይሆን? አሊያም ታላቁ መሪያችን እያሉ አቶ መለስ ዜናዊን በየአጋጣሚው ማሞገስና በሆነው ባልሆነው ስለእሳቸው ክብር መዘመር በተላላኪነት የማያስፈርጅ ይልቁንም የክብር መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ ነገር ግን ከአቶ ገዱና ከቆሙለት አላማ በተለይም ያለ ማንም ጣልቃገብነት ራስን በራስ የማስተዳደር መርህን በጽናት መያዝን መደገፍ ደግሞ ተላላኪ የሚያሰኝ ሁኔታ ተደርጎ መወሰድ እንዳለበት በእነሱው ጠባብ መድረክ ተወስኖ ይሆን?

አንዳንዴ እጅግ በጣም ግርም የሚለኝ ነገር ደግሞ እነዚህ ጥራዝ ነጠቅ የትግራይ ተወላጅ ጸሀፊዎች አንድን ተመሳሳይ ሀሳብ እነሱ ካሉት ምንጊዜም እውነትና ሳይንሳይዊ ሌላው የሚለው ከሆነ ግን በስሜትና በጥላቻ (በትምህክት) ላይ የተመሰረተ

እንደሆነ አድርገው ማሰባቸው በራሱ ሳይንሱ በትክክል ያልገባቸው ብቻ ሳይሆኑ የበታችነት ስሜታቸው እስካሁንም ድረስ ገና ያለቀቃቸው የደናቁርት ስብስብ መሆናቸውን በግልጽ ያመለክታል፡፡

ሆኖም ከብአዴን አመራር ውስጥ የህወሀት ጠንካራ ደጋፊ በመሆን የሚታወቀውን ግለሰብ (አንዳንዶች የትግራይ ተወላጅ እንደሆነ ያምናሉ) በስም በመጥቀስ ጭምር ግርማ ሞገስና ብቃት የተላበሰው ካሳ ተክለ ብርሀን (charismatic and competent Kassa Teklebrehan) ብሎ በመግለጽ ጭምር እናንተ ሰዎች ለምን ይህንን ሰው የህወሀት ተለጣፊ ትሉታላችሁ በማለት ሊሞግተን ይሞክራል፡፡ ለነገሩ በእቶ ብርሀነና መሰሎቹ አልፈርድባቸውም፣ ምክንያቱም አቶ ካሳ በእርግጥም የህወሀትን አላማ ለማስፈጸም ወደ ብአዴን የገባ በመሆኑ የአማራ ተወላጆች ከየክልሉ ሲፈናቀሉ ትንፍሽ ሳይል ቆይቶ የትግራይ ተወላጆች ከጎንደር በተለይም ከሽንፋ ሲፈናቀሉ ከጎናቸው ቆሞ እንባ በማውጣት ጭምር እየየ ማለቱ ይታወቃልና ነው፡፡

ከዛም አልፎ የገዱ አንዳርጋቸው ብአዴን ተጸጽዕኖ ፌዴራል መንግስት ድረስ ዘልቆ በአሁኑ ወቅት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የፌዴራል መንግስት የስራ ሀላፊዎችን እስከ ማፈናቀል የደረሰ መሆኑን በምሳሌ ሲያስረዳ በሞያው ረዥም ጊዜ የሰራውንና የተሻለ ብቃት ያለውን ኢሳያስ ባህረን በብአዴኑ አባልና የመንግስት የፋይናንስ ተቋማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተሩ ዶ/ር ስንታየሁ ወ/ሚካኤል አማካኝነት ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬሲዳንትነቱ ያለ አግባብ እንዲነሳ አደረገ ሲል ይከሳል፡፡ እውነት! ብአዴንም ለዚህ በቅቷል እንዴ ባክህ!! ይኸ የብርሀነ ቅዠት ከሰሞኑ አንዳንድ የትግራይ ተወላጆች በቁጭት ውስጥ ሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን፣ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤትንና የኢትዮጵያ ብሮድ ካስት ኮረፖሬሽንን የእነሱ ሰዎች ለቀው በሌላ መተካቱ ህወሀትንና የትግራይን ህዝብ ለማዳከም ሆን ተብሎ እንደተደረገ ሴራ አድርገው የተለመደ የውንጀላ ሙሾ ማውረዳቸውን ያስታውሰኛል፡፡ በእርግጥ ሲጠባ የለመደ ጥጃ ሲይዙ ይጓጉራል ነውና ነገሩ አይፈረድባቸውም፡፡ 60,000 የሚሆኑ የህወሀት ታጋዮች እንደሞቱና ከ100,000 የማያንሱት ደግሞ የአካል ጉዳተኛ እንደሆኑ ብሎም በህውዜን ከተማ ብቻ 2,500 ሰዎች በግፍ እንደተጨፈጨፉ ነግሮናል፡፡ ይኸ ሁኔታ መድረሱን እኛም የምናወቀው እውነት ቢሆንም እነንደማንኛውም ኢትዮፕያዊ መታየት የለባቸውም ወይ የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል፡፡

ይህም ማለት ሰቆጣ ከተማ ከ11 ጊዜ በላይ ተደብድቦ በመቶዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች አልሞቱም? በለሳ ሀሙሲት፣ መርሳና ሌሎች የአማራ ክልል ከተሞች በአውሮፕላን ተደብድበው በርካቶች ሲሞቱ በሽዎች የሚቆጠሩት የአካል ጉዳት ሰለባ አልሆኑም? በሽዎች የሚቆጠሩ የኢህዴን/ብአዴን ታጋዮች ተሰውተው እኔን ጨምሮ በአስር ሽዎች የሚገመቱት የአካል ጉዳት አልደረሰባቸውም? ወይስ በቀደመው መጣጥፉ አማካኝነት በድፍረት ለማለት እንደሞከረው የትግራይ ህዝብና የህወሀት ታጋዮች ብቻ ናቸው መስዋእትነት ከፍለው ነጻ የወጧችሁ ያሉትን አበክሮ እየደገመልን ይሆን?

እውነት ነው አቶ ብርሀነ ለመግለጽ እንደሞከረው በአማራ ክልል በተለይም ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር የተወሰኑ ወረዳዎች ውስጥ በተፈጠረው ሁከትና ብጥብጥ ሳቢያ የባለ ሀብቶች ንብረት ወድሟል የሰው ህይወትም ጠፍቷል፣ በተመሳሳይ ወቅትና አሁንም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ከዚህ በከፋ መልኩ የንብረት ወድመት ደርሷል፣ በመቶዎች የሚቆጠር የሰው ህይዎት ጠፍቷል፣ ነገር ግን ይኸ ሁኔታ ለአቶ ብርሀነና ለመሰሎቹ አይታያቸውም፡፡ ሌላው በምሳሌነት ያነሳው የዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሔርን ሪፖርት ይዘት የአማራ ክልል መንግስትን ለመወንጀል ሆን ተብሎ የተጠቀሙበት መሆኑን ለማሳየት መሞከሬን መሰረተቢስ ሲሉ ለማጣጣል መጣደፋቸው ነው፡፡

የዚህን ግለሰብ አላማ ለመገንዘብ ካስፈለገ አንድ ምሳሌ በአጭሩ ልክል፣ ግለሰቡ የህወሀትን መሰሪ አላማ ይዞ ወደ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በሀላፊነት ከመግባቱ በፊ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ ሆኖ በሰራባቸው ጥቂት አመታት ውስጥ በህወሀት የሚመራው ኢህአዴግ የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርአትን በሚከተሉ ዴሞክራሲያዊ መንግስታት ዘንድ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በ2007 ዓ.ም በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ 100% በሆነ ውጤት እንዲያሸንፍ በማድረግ ታማኝነቱን ይበልጥ ማረጋገጡ ከታወቀ በኋላ ሳምንት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ አይደለም እንዴ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ሆኖ የተሾመው፡፡ ዶ/ር አዲሱ ራሱ የምርመራ ውጤቱን አስመልክቶ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት የኦሮሚያ ክልልን የመረመርነው በራሳችን ተነሳሽነት ሲሆን ሁከቱን ለማስቆም በመንግስት የጸጥታ አካላት የተወሰደው የሀይል እርምጃም ተመጣጣኝ ነው ነገር ግን የአማራ ክልልን ያጠናነው የተወሰኑ አካላት (ምናልባትም የትግራይ ተወላጆችና የቅማንት ተወካዮች ሊሆኑ ይችላሉ) ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን ብጥብጡንና እያስከተለው የነበረውን ጉዳት ለማስቆም የክልሉ የጸጥታ ሀይል የወሰደው እርምጃም ተመጣጣኝ አይደለም በማለት ነበር ፍርደ ገምድል ማብራሪያ በመስጠት የተለየ አላማ ይዞ መንቀሳቀሱን ያረጋገጠው፡፡

ሌላው መሰረተ ቢስ ሀሳብ የቀረበው በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙ አማሮች ላይ የአጸፋ እርምጃ አለመወሰዱን የተመለከተው ማረጋገጫ ነው፣ በነገራችን ላይ በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙትና በመቶ ሽዎች የሚገመቱት የአማራ ብሔር አባላት በህወሀት ጠባብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተው አከላለል ያለ ፍላጎታቸው ወደ ትግራይ አስተዳደር በማስገባት ሰለባ ያደረጋቸው የወልቃይት-ጸገዴና የራያ አካባቢ ነባር ነዋሪዎች በራሳቸው መሬት የሚኖሩ እንጂ ለስራ ወይም ለሌላ አላማ ወደ ትግራይ ክልል ተሰደው የሄዱና በትግራዮች መሬት ላይ ሰፍረው በጥገኝነት የሚኖሩ እንዳልሆኑ አቶ ብርሀነ የተገነዘበ አይመስለኝም፡፡

በሌላ አነጋገር እነዚህ በአሁኑ ወቅት ትግራይ ክልል እየተባለ በሚጠራው ደቡባዊ ድንበር አካባቢ የሚገኙት አማሮች እኮ ከአያት ቀድመ አያተቻቸው ጀምሮ ለዘመናት በኖሩበት በራሳቸው መሬት ላይ የሚገኙ እንጂ በስደት መልክ ወደ አካባቢው ሄደው የሰፈሩ ሰዎች አይደሉም፡፡ የሚገርመው ነገር እነዚህ አማሮች የሚገኙት በዋነኛነት በትግራይና በአማራ ክልሎች ድንበር ሆኖ ሳለ መሬቱ ለም፣ አካባቢው እጅግ በጣም ምርታማ ሆኖ በመገኘቱ ብቻ ለትግራይ ክልል አስፈላጊ ነው ተብሎ የተከለለ ከመሆኑም በላይ በሰላሙ ጊዜ ሳይቀር ነዋሪዎቹንን ከፈለጋችሁ ወደ አማራ ክልል ሄዱ እንደሚባሉ አቶ ብርሀ አልሰማ ይሆን?

ከሀገራችን የቀደመም ሆነ የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደምንገነዘበውም ስደት በአብዛኛው ከሰሜኑ ጫፍ የሀገራችን ክፍል ወደ መሀልና ደቡቡ የሀገራችን ክፍል እንጂ ከመሀልና ከደቡብ ወደ ሰሜን ምናልባትም በ16ኛ መቶ ክ/ዘመን ከኦሮሞዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ሊነሳ ከሚችል ክስተት (ይኸውም ቢሆን ኦሮሞዎች ወደ ቀደመ ቦታቸው ለመመለስ ያደረጉት ጥረት እንደሆነ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየወጡ ያሉ የምርምር ስራዎች በግልጽ ያመለክታሉ) እንዲሁም የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ሲባል የመሀል አገሩና የደቡቡ አካባቢ ኢትዮጵያዊ ጦር ሰብቆ ሲዘምት ካልሆነ በስተጠቀር ስራና እንጀራ ፍለጋ ወደ ትግራይ ምድር ሲሄድ አይተንም ሆነ ሰምተን አሊያም አንብበን አናውቅም፡፡ ታዲያ አቶ ብርሀነ ደጋግሞ ሊነግረን እንደሚሞክረው በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙት አማሮች ላይ የትግራይ ክልል መንግስትም ሆነ ህወሀትና ደጋፊዎቹ የአጸፋ እርምጃ አልወሰዱም፣ ይህም የሆነው የትግራይ ህዝብ አስተዋይና የተከበረ ስለሆነ ነው ማለቱ ከየት የመጣ ተረት-ተረት ይሆን? የዚህ አይነት አይን አውጣነት ሲገጥመው የአገሬ ሰው ብጥለው ገለበጠኝ ወይም ጅራፍ ራሷ ገርፋ ራሷ ትጮሀለች ይላል፡፡

እስቲ አቶ ብርሀነ በነካ አፍህ ከላይ ከተጠቀሱት አካባቢዎች ውጭ ማለትም አድዋ፣ አዲግራት፣ አክሱም ሀውዜን፣ ተምቤን ወይስ የትኛው የትግራይ ገጠር ወይም ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አማሮችን ለማለት ፈልገህ ነው ደጋግመህ ለማስታወስ ያውም በንጽጽር መልክ የትግራይን ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የበለጠ ጀግና፣ ታጋሽና የሰለጠነ አድርገህ ለማቅረብ የሞከርኸው? ስለሆነም ይኸ በመታበይ ላይ የተመሰረተ ውንጀላ ይበቃል ሊባል የሚገባውም የአንተውና የመሰሎችህ እንጂ በመረጃ ላይ ተመስርተው እውነታውን ለማቅረብ በሞከሩት ኢትዮጵያዊያን ላይ ሊሰነዘር የሚችል ማስፈራሪያ ሊሆን አይገባውም፡፡

ያም ሆነ ይህ አላስፈላጊውን መወነጃጀል ትተን በተለይም ከእንደዚህ ካለ በመታበይ ላይ የተመሰረተ አዙሪትና ክፉ ሀሳብ ወጥተን ቀና ቀናውን ብናስብና ከዚህ እጅግ ጠባብ ከሆነ አስተሳብ ተላቀን የጋራ ሀገራችን የሆነችውን ኢትዮጵያን ለማሳደግ ብሎም ህዝቦቿም ከዕድገቱ እኩልና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ብንጥር? ይህ ሲሆን ይመስለኛል በእርግጥም ለእውነተኛ አንድነት የቆምን፣ ለዘላቂ ብልጽግናና መሻሻል የምንሰራ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መሆናችንን ማሳየት የምንችለው፡፡

እውነት ያሸንፋል!

መልካም ንባብ!!